ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

ቀን ግንቦት 20 2000 ዓ.ም

## የተበከለ ዘይት ሰው እየፈጀ ነው፡፡ ጥቁር አንበሳና ፓስተር ሆስፒታሎች በበሽተኛ ተጨናንቀዋል፡፡

ማክሰኞ ግንቦት 19 2000 ከአዲስ አበባ የደረሰን ዘገባ እንደሚያመለክተው በተበከለ ዘይት ተመርዘው የሞቱትና የታመሙት የከተማው ኗሪዎች በርካታ መሆናቸውን ነው፡፡ በሰኞ እለት ምሽት የፓስተርና የጥቁር አንበሳ ሆስፒታሎች በዘይቱ ተመርዘው በሚሰቃዩ በሽተኞች ተጨናንቀው ታይተዋል፡፡ ለእዚህ የተመረዘ ዘይት ሰለባ የሆኑት የከተማ ዜጎች አብዛኛዎቹ የሚኖሩት አዲሱ ሚካኤል በሚባለው በአዲስ ከተማ አካባቢ እንደሆነ ታውቋል፡፡ ይህ አይነቱ የምግብ ዘይትና ሌላም የሚበላ ነገር ምረዛ የኑሮ ውድነት የሚያሰቃየውንና ሸቀጥ ለመግዛት አቅሙ የሌለውን ደሃ የህብረተሰቡን ክፍል እንደሆነ በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡ ከእዚህ ጋር ተያይዞ የደረሰን ዜና ዳቦ በከተማው መጥፋቱንና የከተማው መብራት ከሚሰራበት ግዜ የበለጠ የማይሰራበት ግዜ እየበለጠ እየሆነ በመሄድ ላይ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ከቁጥጥር ውጭ በመውጣት ላይ ያለ የኢኮኖሚ ቀውስ መዘዙ የሚስፈራ ሊሆን እንደሚችል የሚገምቱ ብዙ ናቸው፡፡ የተራበ ህዝብ መንግስቱን ይበላል በማለት በቅርቡ ዶ/ር መራራ ጉዲና በምክር ቤቱ የተናገሩት ቃል እውን ሊሆን ይችላል በማለት ስጋት የገጠማቸው የመንግስት ካድሬዎችና ከአነሱ ጋር ጡት የተጣቡ የዘመኑ ሃበታሞች ገንዘብ በብዘት ወደ ውጭ ማሸሽ መጀመራቸው ይነገራል፡፡